| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ታሪካዊ ፡ አደጋ ። " |
| ደራሲ ፤ | ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፤ | መጋቢት ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-004 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## ታሪካዊ ፡ አደጋ ።

---

ወገንን ፡ ከወገን ፡ ያራራቀ ፥ ሀገርን ፡ ከሀገር ፡ ያፈራቀቀ ፥ መነሻው ፡ ያልታወቀ ፡ ምስጢር ፥ መድረሻው ፡ የማይታወቅ ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማ ፥ የ"ኮቪድ-19" ፡ ዓለም ፡ ዐቀፍ ፡ ወረርሽኝ ፥ ደካማ ፣ ኀያል ፡ ሳይል ፥ ኹሉን ፡ ሊያደቅና ፡ ሊያንኰታኵት ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ ታሪካዊ ፡ አደጋ ፡ ነው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ በዐላማ ፡ ተባብሮና ፡ ከሥራ ፡ ተሳትፎ ፡ ይህን ፡ የመከራ ፡ ወቅት ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ ሊሻገረው ፡ ይገባል ። ለዚህም ፡ ዋነኛው ፡ ስልት ፡ ለሕግና ፡ ለሥርዐት ፡ የኹሉም ፡ መገዛት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አፍራሻውን ፡ ግፍንና ፡ በደልን ፡ በማናለብኝነት ፡ የሚፈጽሙትን ፡ ኹሉ ፥ የዓለም ፡ ኅብረተሰብ ፡ ለራሱ ፡ ሲል ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ሐይ ፡ ሊላቸው ፡ ይገባል ። ይህን ፡ ባይፈጽም ፡ ግን ፥ ለደኅንነቱ ፡ ዋስትና ፡ አይኖረውም ። የኮቪድ-19 ፡ ወረርሽኝ ፡ በጤና ፡ መታወክ ፡ ብቻ ፡ የማይወሰን ፥ አጠቃላይ ፡ ጥርየታዊና ፡ ስያሳዊ ፣ ማኅበራዊና ፡ ጸጥታዊ ፡ መናጋትን ፡ በማስከተል ፥ ለዓለም ፡ ሰላም ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ጠንቅ ፡ ይኖረዋል ።

ያሳዝናል ፤ በኢትዮጵያ ፡ የታየው ፡ ኹኔታ ፡ የአጥፊነት ፡ ኾኗል ። ሥርዐትን ፡ ወደ ፡ ማክበርና ፡ ማስከበር ፡ ያመራ ፡ ይኾናል ፡ ተብሎ ፡ ባይጠበቅም ፥ ባይኾን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፥ የጥፋት ፡ ግብሩን ፡ ይገታል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ የተደረገበት ፡ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.-ብልጽግና ፡ ፓርቲ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፥ አፍራሻውን ፡ ጭልጥ ፡ ብሎ ፡ በጥፋት ፡ አግጣጫው ፡ በመቀጠል ፥ የራሱን ፡ ሥርዐትም ፡ እንኳ ፡ እየጣሰ ፥ በኢትዮጵያ ፡ መሠረታውያን ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ የጠላትነት ፡ ውሳኔዎቹን ፡ በመፈጸም ፡ ሀገርን ፡ መበደሉን ፡ ቀጥሏል ።

ከነዚህ ፡ የጠላትነት ፡ ውሳኔዎች ፡ ውስጥ ፡ የሐራ ፡ ሀገርነት ፡ ተምሳሊት ፡ የኾነውን ፡ ሀገራዊ ፡ ልሳናችን ፡ ዐማርኛን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ አንጻር ፡ የበታች ፡ የማድረግ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ውሳኔው ፡ ነው ።

ዐማርኛ ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ በደለ ፧ ሰውን ፡ ከሰው ፡ ባግባባ ፧ ሀገርን ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ባገናኘ ፧ ሥልጣኔን ፡ ባስፋፋ ፧ ሥርዐትን ፡ ባጸና ፧ የኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ ተማሪ ፡ ታሪኩን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ይማረው ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ ለየትኛው ፡ ጥቅም ፡ ነው ፧ ማንንስ ፡ ለማስደሰት ፧ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ልሳን ፡ ዐማርኛ ፡ እያለልን ፥ ካማርኛ ፡ ጋራ ፡ ዐምስት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ቋንቋዎች ፡ ይኑሩን ፡ ብሎ ፡ 84 ፡ የውልደት ፡ ቋንቋዎች ፡ ባሉበት ፡ ሀገር ፡ መወሰንስ ፡ ፍትሓዊነቱ ፡ ምኑ ፡ ላይ ፡ ነው ፧ ደግሞስ ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ ባ5ኛ ፡ አንቀጹ ፡ ዐማርኛ ፡ "የደባዩ ፡ መንግሥት ፡ የሥራ ፡ ቋንቋ" ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አጽድቆታል ፡ ያሉንን ፥ ከመቼው ፡ ዐጥፈውት ፥ ሥልጣን ፡ በሌለው ፡ አገዛዝ ፡ ውሳኔ ፡ ዐማርኛን ፡ ለመሻር ፡ ተቻኰሉ ፧

ለእነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፡ ብሎ ፡ እንደማይጠበቅ ፡ ኹሉ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፥ ዐይኑ ፡ እያየ ፡ ሀገሩን ፡ ይነጠቃል ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ ነው ።

ፀረ ፡ ዐማርኛ ፡ ስያስ ፡ ፀረ ፡ ሀገር ፡ ስያስ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይህ ፡ ፀረ ፡ ዐማርኛ ፡ ውሳኔ ፡ ያጠቃላዩ ፡ የሀገር ፡ ፈረሳ ፣ የ"ዩጎስላቪዜሽን" ፡ ዕቅድ ፡ የማዕዘን ፡ ድንጋይ ፡ ነውና ፥ ሕዝብ ፡ አጥብቆ ፡ ሊዋጋው ፡ ይገባል ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ የከፋፈለ ፥ ምድሯንም ፡ የገነጣጠለ ፥ ሀብቷን ፡ የበዘበዘና ፡ ያስበዘበዘ ፥ ከዋጋ ፡ ንረት ፡ ሌላ ፡ እድገትን ፡ ያላመጣ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ግብርና ፡ ከበሬ ፡ ጫንቃ ፡ ያላወረደ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፥ ቋንቋ ፡ በማብዛት ፡ ልማትን ፡ አመጣለኹ ፡ ሲለን ፡ በፍጹም ፡ አንቀበለውም ❖

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
ኢ. ሀ. ሥ. አ.
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።